# <u>በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ካሉ ሴቶች ሕይወት መማር</u>

<u>የታሪኮች ዝርዝር</u>

1. ማርታ፡- እንግዳ ተቀባይ
2. ማሪያም፡- የሚቀድመውን የሚታውቅ
3. ማሪያም፡- መሪ
4. ሃና፡- የእግዚአብሔር ታላቅ ዕቅድ የተከናወነባት
5. ሔዋን፡- የተሳሳተች
6. ሔዋን፡- የስህተታችን ታሪክ
7. ዶርቃ፡- የአገልጋይ ልብ የነበራት ሴት
8. አብጋል፡- የሰላም ሴት
9. አጋር፡- እግዚአብሔር ስቃይህን ያያል
10. ሣራ፡- የእምነት ሰው
11. እርብቃ፡- እግዚአብሔርን ሰምታ የታዘዘች ሴት
12. እርብቃ፣ሁለተኛው ክፍል፡- እግዚአብሔር ዕቅዱን እንዲፈጽም በእርሱ ላይ መደገፍ
13. የሳምሶን እናት፡- በጋብቻ ፍቅርና አክብሮት የነበራት ሴት
14. ሩት፡1፡- ሩትና ኑኃሚን
15. ሩት፡2፡- ሩትና ኑኃሚን
16. ሩት፡3፡- ሩትና ኑኃሚን
17. ሩት፡4፡- ሩትና ኑኃሚን
18. መግደላዊት ማሪያም፡- ይቅር የተባለላት
19. ረአብ፡- እግዚአብሔርን ያከበረች ሴት
20. የአንድነትና የፀሎት ሳምንት፡- ይህንን የጥናት ጊዜ እንደገና ገምግሙ፡፡ በሕይወትህ እንዴት ለውጥ እንደመጣ ለቡድንህ አባላት አካፍል፡፡

<u>በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ካሉ ሴቶች ሕይወት መማር</u>

እኔና ባለቤቴ ዶ/ር አንድረሰን (Dr. Anderson) በ1997 ዓ.ም ወደ ኢትዮጵያ መጣን፡፡ እኔ መጽሐፍ ቅዱስን በቁጥር አነስተኛ ለሆኑ ሴቶች ቡድን ማስተማር ጀመርኩ፡፡ የእግዚአብሔርን ቃል በማጥናታችን ደግሞም እንዴት መልካም ምስቶች፣ሴቶችና ጓደኞሞች መሆን እንደምንችል በመማራችን በጣም ጥሩ ጊዜ አሳልፈናል፡፡ በዚህ ባሳለፍነው ዓመት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስላሉ ሴቶች ተምረን ነበር፡፡ ከእነዚህ ሴቶች ሕይወት ብዙ ተምረናል፣ እናንተም መማር ትችላላችሁ፡፡

ለቡድን መሪዎች ጥቅት የሚለው አለኝ፡-

- መምራት ትችላለህ፡፡ ለመምራት ብዙ ዕውቀት ባይኖርህ አትጨነቅ፡፡ ፀልይ መንፈስ ቅዱስ ቡድንህን ይረዳል፡፡
- ሁሉም ሴቶች እንዲናገሩ አበረታታቸው፡፡ እያንዳንዱ ሰው የሚለው አለው፡፡
- መርነቱን ተከፋፈሉ፡፡ ሌሎችም ቡድኑን እንዲመሩ ዕድል ስጣቸው፡፡
- ታሪኩን ስትናገር ቃል በቃል ለመናገር አትሞክር፡፡ ዋና ነጥቦችን ብቻ መላልሰህ በማጥናት ከአእምሮህ ለመናገር ሞክር፡፡ ዋና ነጥቦችን በአእምሮህ ለመያዝ ክፍሉን ደጋግመህ ማንበብ አለብህ፡፡ ከዚያም ታሪኩን ለብቻህ ተለማመድ፡፡

- ታሪኩ በሚነገርበት ጊዜ መጽሐፍ ቅዱስ ዝግ መሆን አለበት፡፡ ታሪኩን የሚናገረው ሰው የእያንዳንዱን ሰው ፊት እያየ መናገር አለበት፡፡
- በመቀጠል ‹‹በመጀመሪያ ምን ሆነ?, ከዚህ በኋላ ሔዋን ምን አለች?, ቀጥሎ ምን ሆነ?, ሰይጣን ምን አለ?>> እነዚህን የመሳሰሉ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ታሪኩን የበለጠ ግልጽ አድርግ፡፡
- እነዚህ ጥያቄዎች የቡድኑ አባላት በውይይቱ እንዲሳተፉና ታሪኩን እንዲያስታውሱ ይረዳሉ፡፡ ማን? ምን? መቼ? ዬት? እና እንዴት? የሚሉት መሠረታዊ የምልከታ ጥያቄዎች ናቸው፡፡
- ከዚያም መጽሐፍ ቅዱሳችሁን አውጥታችሁ ታሪኩን አንብቡ፡፡ ታሪኩ በቃል ሲነገር የቀረ ወይም የተጨመረ ነገር ካለ ታሪኩ በሚነበብበት ጊዜ የቡድኑ አባላት እንዲያዳምጡ አድርግ፡፡ ታሪኩ በሚነገርበት ጊዜ የግድ አንድም ሳይቀር መነገር አለበት አይባልም፡፡ ምክንያቱም ታሪኩ በኋላ ስለሚነበብ፡፡
- ታሪኩን ለመረዳትና ከሕይወት ጋር ለማዛመድ የውይይት ጥያቄዎችን ተጠቀም፡፡

እግዚአብሔር ይባርካችሁ፡፡
ከጃኪ አንደርሰን (Jackie Anderson)

<u>አንደኛ ሣምንት</u>
<u>ከመጽሐፍ ቅዱስ ሴቶች ሕይወት መማር</u>
<u>ማርታ፡- ሉቃ፡10፡38-42</u>
<u>ታሪኩ፡- ቅድሚያ ስለሚያስፈልገው ነገር ያወራል፡፡</u>
<u>መግቢያ</u>፡- ማርታ የማሪያምና የአልዓዛር ታላቅ እህታቸው ነች፡፡ ማሪያምና ማርታ ሁለቱም ኢየሱስን ይወዱት ነበር፡፡ ቤታቸው እርፍት የሞላበት ስለነበረ ኢየሱስ ሊጎበኘው ፈለገ፡፡ ማሪያምና ማርታ በእንግዳ ተቀባይነታቸው የታወቁ ሰዎች ነበሩ፡፡ ታሪኩ ቀጥሎ ቀርቧል፡-
ታሪኩን ተናገር፡፡ ታሪኩን አንብብ፡፡
<u>የሚከተሉትንና ሌሎችን ጥያቄዎችን በመጠየቅ ታሪኩን የበለጠ ግልጽ አድርግ</u>

1. ቤቷን ለኢየሱስ የከፈተችው ማን ነበረች?
2. ማሪያም ምን ታደርግ ነበር?
3. ማርታ ምን ታደርግ ነበር?
4. ማርታ ምን አለች?
5. ኢየሱስ ምን አለ?

<u>የውይይት ጥያቄዎች</u>

1. ማርታ ያደረገችው ምን ነበር? ለዚህ ጠንካራ ጎኑ ምንድነው?
2. የማርታ ደካማ ጎን ምን ነበር?
3. ኢየሱስ የማርታ ሥራ አስፈላጊ አይደለም አላለም:: እሷ ምን እንዲታደርግ ነው ኢየሱስ የጠየቀው?
4. ከዚህ ታሪክ ስለ ኢየሱስ ምን እንማራለን? ኢየሱስ ለማርታ ፍቅሩን እንዴት ገለጠ?

5. እኛ ስናገለግል አመለካከታችን ምን መሆን አለበት? 1ጴጥ፡4፡9
6. ቅድሚያ ስለሚያስፈልገው ነገር ከማርታ ሕይወት ምን እንማራለን? አንተም እንደማርታ ለኢየሱስ እያገለገልኩ ነው እያልክ እየባከንክ ነህ ወይስ እንደማሪያም ከእሱ ጋር የምትነጋገርበት ጊዜ አለህ? ከዚህ ታሪክ የተነሣ ሕይወትሽ እንዴት መቀየር አለበት?

ሁለተኛ ሣምንት

ከመጽሐፍ ቅዱስ ሴቶች ሕይወት መማር

የማርታ እህት፣ማሪያም፡ ሉቃ፡10፡38-42

ታሪኩ፡- ቅድሚያ ስለሚያስፈልገው ነገር ያወራል፡፡

መግቢያ፡- ባለፈው ሳምንት ስለ ሁለት እህትማማቾች ተምረን ነበር፡፡ ማርታ ኢየሱስን ወደ ቤቷ የተቀበለች ታታሪ ሠራተኛ ነበረች፡፡ በዚህ ሣምንት የማርታ እህት ስለሆነችው ማሪያም እንማራለን፡፡

ከቡድንህ ውስጥ አንድ ሰው ታሪኩን እንዲናገር አድርግ፡፡

የውይይት ጥያቄዎች፡-

1. የማሪያም ጠንካራ ጎን ምን ነበር? በዚህ ታሪክ ውስጥ ደካማ ጎኗስ ምን ነበር?
2. ኢየሱስ ሌሎችን ስለማገልገል አስፈላጊነት አስተምሯል፡፡ በዚህ ታሪክ ውስጥ ኢየሱስ ሊያስተምረን የፈለገው ምንድነው?
3. በቁ፣42 ላይ ‹‹አስፈላጊው ነገር›› ምንድነው?
4. ማሪያም የት ነበር የተቀመጠችው? በደቀመዛሙርቶች ዘመን ባሕል መሠረት ይህ ቦታ ወንድ ደቀመዝሙር የሚቀመጥበት ቦታ ነበር፡፡ በባሕሉ መሠረት ከሆነ ማሪያም እንግዳ መቀበል ነበረባት፡፡ እዚህ ጋ ኢየሱስ የሚያስተምረን ምንድነው?
5. በዮሐ፣12፡1-8 ባለው ሥፍራ ማሪያም ውድ በሆነ ሽቱ የኢየሱስን እግር እንዳበሰችው እንመለከታለን፡፡ ከኢየሱስ እግር ሥር ሆነህ ቃሉን በመስማት ለእርሱ ምላሽ ትሰጣለህ? ደግሞም በሕይወትህ ኢየሱስን የምታመልክበትን መንገድ ትፈልጋለህ? ስለ ኢየሱስ የበለጠ ስንማር አምልኳችን እንዴት እንደሚጨምር ተወያዩ፡፡
6. በዚህ ሣምንት ለሕይወትህ ምን ትማራለህ?

አስተያየት፡- በኢየሱስ ዘመን ዋናው ምግብ የሚበላበት ጊዜ ማታ ነበር፡፡ የተለመደው ምግብ የምስር ወጥ በርበሬ ከሚመስል ተክል ጋር መብላት ነው፡፡
ልክ በኢትዮጵያ እንደሚደረገው ወንዶች ለመብላት ሲቀመጡ ሴቶች ያስተናግዱ ነበር፡፡ በእጆቻቸው ይበሉ ነበር፡፡ እንዲሁም የፍየል አይብ፣የዝግባ ፍሬና ዳቦ ሌላው ምግባቸው ነበር፡፡ የዘንባባ ፍሬም ይመገቡ ነበር፡፡

ሦስተኛ ሣምንት

ከመጽሐፍ ቅዱስ ሴቶች ሕይወት መማር

ማሪያም ዘፀ፡2፡1-10 እና ዘኁል፡12

ታሪክ፡- የሴቶች መሪ

መግቢያ፡- የእግዚአብሔር ሕዝብ በግብፅ በባሪነት ቀንበር ሥር ነበሩ፡፡ ብዙ እሥራኤላዊያን እየተዋለዱ በሄዱ ጊዜ ፈርኦን እጅግ ፈራ፡፡ ስለዚህ አዲስ የሚወለዱ ወንድ ልጆች በሙሉ በናይል ወንዝ እንዲጣሉ ትዕዛዝ አወጣ፡፡ ነገር ግን አንዲት እናት ልጇን ደበቀችው፡፡ የሙሴ እህት የማሪያም ታሪክ ከዚህ ቀጥሎ ቀርቧል፡፡ እሷ እግዚአብሔር የተጠቀማት ሴትና ጠንካራ መሪ ነበረች፡፡ ነገር ግን እሷም የራሷ የሆነ ችግር ነበራት፡፡ የዛሬው ታሪክ በሁለት ክፍል የተከፈለ ነው፡፡

የመጀመሪያው ክፍል ከዘፀአት እንደሚከተለው ቀርቧል፡-

በዘፀ፡2፡1-10 ያለውን ታሪክ ተናገር፡፡

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በመጠየቅ ታሪኩን የበለጠ ግልጽ አድርግ፡፡

1. የሙሴ እናት ሙሴን የት ደበቀችው? ቀጥሎ ምን እንደሚሆን በቅርብ ርቀት ትከታተል የነበረችው ማን ነበረች?
2. የፈርኦን ሴት ልጅ በመጣች ጊዜ ምን ሆነ?
3. ማሪያም ምን አደረገች?
4. ቀጥሎ ምን ሆነ?

ታሪኩን አንብብ፡፡

ከብዙ ዓመታት በኋላ የእሥራኤል ሕዝብ ከፈርኦን ባርነት ነፃ ወጣ፡፡ በእግዚአብሔር እርዳታ ወደ ምደረ በዳ መጣ፡፡ ዘፀ፡15፡20-21 አንብብ፡፡ ማሪያም የሴቶች መሪ ነበረች፡፡ እግዚአብሔርን ታመልክ ነበር፤ሙሴንና አሮንን ትረዳቸው ነበር፡፡

ሁለተኛው የታሪኩ ክፍል ቀጥሎ ቀርቧል፡-

ዘኀል፡12 ላይ ያለውን ታሪክ ተናገር፡፡

የሚከተሉትንና ሌሎችን ጥያቄዎች በመጠየቅ ታሪኩን የበለጠ ግልጽ አድርግ

1. በመጀመሪያ የሆነው ነገር ምን ነበር?
2. ለሶስቱ ሰዎች እግዚአብሔር ምን አለ? እግዚአብሔር እንዴት መጣ?
3. እግዚአብሔር ከሙሴ ጋር እንዴት ተነጋገረ?
4. ማሪያምና አሮን በሙሴ ላይ ስለተናገሩት ንግግር እግዚአብሔር ምን አለ?
5. ማሪያም ምን ሆነች?
6. በኋላ አሮን ሙሴን ምን አለው? ሙሴ እግዚአብሔርን ምን አለው?
7. ቀጥሎ ምን ሆነ? ሕዝቡ ምን አደረገ?

የውይይት ጥያቄዎች

1. ማሪያም የፈርኦንን ሴት ልጅ እንዳትቀርባት አደገኛ የሆነው ለምንድነው? ይህ ስለ ማሪያም ምን ያስተምረናል? ምንም እንኳ የሚያስፈራ ነገር ቢኖርም አጋጣሚዎችን ስለመጠቀም ከዚህ ታሪክ ምን እንማራለን?
2. በቁ፣3 መሠረት ሙሴ ምን ዓይነት መሪ ነበር?
3. ሙሴ ከሁሉም ታናሽ ነው:: በተለምዶ አነጋገር ሙሴ በታላቅ ወንድሙና እህቱ ላይ ስልጣን ሊኖረው ይችላል? ምናልባት ችግሩን ካመጡት ነገሮች አንዱ የእሱ ባለሥልጣን መሆን ይመስልሃልን?
4. ማሪያም ሙሴን ለምን ወቀሰችው? በልቧ የነበረው ሃሳብ ምን ነበር?
5. አዋቂ እንደመሆኗ መጠን ስለማሪያም ምን እንማራለን? ጠንካራና ደካማ ጎኖቿ ምን ነበሩ?
6. አንተ መሪ ነህ? በመሪነትህ በሰዎች ለመታወቅና  የበለጠ ስልጣን ለማግኘት ብለህ ጥረት አድርገህ ታውቃለህ?
7. ከዚህ ታሪክ ዛሬ ምን ትማራለህ?

አራተኛ ሣምንት

ከመጽሐፍ ቅዱስ ሴቶ ሕይወት መማር

ሃና፣1ሳሙ፡1

ታሪክ፡- የእግዚአብሔር ታላቅነትና ፀሎት

መግቢያ፡- የእሥራኤል ሕዝብ በተስፋይቱ ምድር ለብዙ ዓመታት ኖረ፡፡ በዚህ ጊዜ ሕዝቡ በእግዚአብሔር ላይ አምፀው ሌሎችን አማልክት አመለኩ፡፡ ከዚህ የተነሣ እግዚአብሔር ሌሎችን ሕዝቦች ልኮ የአይሁድን ሕዝብ እንዲገዙአቸው አደረገ፡፡ ሕዝቡ ንስሐ ከገቡ በኋላ እግዚአብሔር መስፍን ልኮ አዳናቸው፡፡ መስፍን በእግዚአብሔር ፊት ትክክልና ትክክል ያልሆነውን ለሕዝቡ የሚያስተምር መሪ ነበር፡፡ ይህ ታሪክ የእግዚአብሔር ሕዝብ አማልክትን ሲከተሉ እግዚአብሔር ስለተጠቀማት አንዲት ሴት ይናገራል፡፡

1ሳሙ፡1 ላይ ያለውን ታሪክ ተናገር፡፡

የሚከተሉትንና ሌሎችን ጥያቄዎች በመጠየቅ ታሪኩን የበለጠ ግልጽ አድርግ፡፡

1. ታሪኩ ስለማን ይናገራል?
2. ሕልቃና በየዓመቱ ዬት ይሄድ ነበር? ሄዶ ምን ያደርግ ነበር?
3. ሕልቃና ለእግዚአብሔር የሚሰዋበት ጊዜ ሲደርስ ምን ያደርግ ነበር?
4. ሃና ለምን አዘነች? ቀጥሎ ምን አደረገች? እሷ ለእግዚአብሔር የገባችው ቃል ኪዳን ምን ነበር?
5. ቀጥሎ ምን ሆነ? ሃና ልጇን ምን አደረገችው?

ታሪኩን አንብብ፡፡

የውይይት ጥያቄዎች

1. በዚህ ታሪክ የነበሩት ስሜቶች ምንድናቸው?
2. ስለ ሴቶች ምን እንማራለን?
3. ስለ እግዚአብሔር ምን እንማራለን?
4. በታሪኩ ውስጥ ካሉት ስሜቶች ወይም ሰቶች የትኛውን ትመስላለህ? በሌሎች ሴቶች ላይ ቀንተህ ታውቃለህ? ለእነሱ ያለው ነገር ለአንተ እንዲኖርህ ፈልገህ ስትፀልይ እግዚአብሔር ፀሎትህን ያልመለሰበት ጊዜ አለ?
5. ስለ ፀሎት ምን እንማራለን?
6. እግዚአብሔር የሚያስተምረኝ ምንድነው? ከዚህ ታሪክ የተነሣ ሕይወቴ እንዴት መለወጥ አለበት?

አስተያየት፡- እግዚአብሔር ፀሎትን በራሱ ጊዜና በራሱ ዕቅድ መሠረት እንደሚመልስ አስቡ፡፡ ለሃና እግዚአብሔር ወዲያውኑ ልጅ ሊሰጣት ይችል ነበር፡፡ ነገር ግን ሃና ልጇን ለእርሱ እንድትሰጠው ፈለገ፡፡ ሳሙኤል ሕዝቡን ወደ እውነት እንዲመራቸው እግዚአብሔር ፈለገ፡፡ ሕዝቡ መሪ ስላስፈለጋቸው ሳሙኤል ታላቅ መሪ ሆነ፡፡ እግዚአብሔር ለሕይወታችን ዕቅድ አለው፡፡ ስለዚህ እግዚአብሔር እንደፈቃዱ በወደደ ጊዜ ፀሎታችንን እንዲመልስ መፀለይ አለብን፡፡

አምስተኛ ሣምንት

ከመጽሐፍ ቅዱስ ሴቶች ሕይወት መማር

ሔዋን፡ ዘፍ፡3፡1-13

ታሪክ፡- መሳሳት (ፈተና) ምን እንደሆነ መረዳት

መግቢያ፡- የመጀመሪያዋ ሴት ስለሆነችው ሔዋን ብዙ የምናውቀው ነገር የለም፡፡ ቢሆንም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ካለው ታሪኳ ብዙ የምንማረው ነገር አለ፡፡ ሰይጣን በእባብ መልክ መጥቶ ሔዋንን እንዴት እንዳሳሳታትና ከእሷ የተነሣ የፍጥረት ታሪክ እንዴት እንተለወጠ ዛሬ እናያለን፡፡ ታሪኩ ቀጥሎ ቀርቧል፡-

ታሪኩን ተናገር፡፡

የሚከተሉትንና ሌሎችን ጥያቄዎች በመጠየቅ ታሪኩን የበለጠ ግልጽ አድርግ፡፡

- በመጀመሪያ ምን ሆነ? ቀጥሎ ምን ሆነ?

ታሪኩን አንብብ፡፡ ታሪኩ ሲነገር የቀረ ነገር ካለ ጠይቃቸው፡፡

የውይይት ጥያቄዎች

1. ሰይጣን ለምን ሔዋንን አሳሳታት? እኛንስ ለምን ያሳስተናል?
2. ሰይጣን እንዴት ሔዋንን አሳሳታት? ምን አላት? ሔዋን በመጨረሻ የነበራት ጥርጣሬ ምን ነበር? ይህ ዛሬ ለእኛ አስፈላጊ ትምህርት የሚሆነው እንዴት ነው?
3. ሔዋን ፈተናውን ለመቋቋም ማድረግ የምትችለው ምን ነበር?
4. ከፈተናና ከማታለል ራሳችንን ለመጠበቅ ማድረግ የምንችለው ምንድነው?
5. በሐጢአት ስንወድቅ ግንኙነታችን ምን ይሆናል?
6. ስለ እግዚአብሔር ምን እንማራለን?
7. የሔዋን ታሪክ ስለተማርክ በዚህ ሣምንት ምን ማድረግ አለብህ?

ስድስተኛ ሣምንት

ከመጽሐፍ ቅዱስ ሴቶች ሕይወት መማር

ሔዋን፡ ዘፍ፡3፡1-13

ታሪክ፡- መሳሳት (ፈተና) ምን እንደሆነ መረዳት

ምናልባት የባለፈውን ሣምንት ታሪክ መናገር የሚችል ሰው ካለ ጠይቅ፡፡

የውይይት ጥያቄዎች

1. በዚህ ሣምንት ይህንን ታሪክ ለጓደኛው የተናገረ ሰው ካለ ጠይቅ፡፡ ምን ሆነ?
2. በዚህ ሣምንት ስለዚህ ታሪክ አስበሃል? ምን ተማርክ?
3. ሐጢአት ልትሠራ የተፈታተንክበትን ጊዜ አስብ፡፡ ሰይጣን ነው ያታለለህ? እንዴት? በሐጢአት ስትፈታተን ውጤቱ ምንድነው? ይህንን ለቡድንህ አባላት አካፍል ተወያይ፡፡
4. የኢትዮጵያ ሴቶች የሚታለሉት በምንድነው?
5. የኢትዮጵያ ሴቶች የሚፈታተኑት በምንድነው?
6. ከዚህ ጥናት የተነሣ በሕይወትህ እንዴት ለውጥ ይመጣል?

አስተያየት፡- ሰይጣን ዛሬም ሴቶችን ለማሳሳት ይፈልጋል፡፡ እሱ የውሸት አባት ነው፡፡ በእናንተ ውስጥ ያለውን ጥርጣሬ እርሱ ያያል፡፡ ከዚያም የእግዚአብሔርን ቃልና

ለእናንተ ያለውን ፍቅሩን እንድትጠራጠሩ ያደርጋል፡፡ የሐጢአት ዋጋ ከእግዚአብሔር ጋር ያላችሁን ግንኙነትና እምነት ማጥፋት ነው፡፡ ጥበበኛ ሴት ሁል ጊዜ ሃሳቧን ትመረምራለች፤እውነትንም ትፈልጋለች፡፡ የእግዚአብሔርን ቃል ማወቅ መልካሙን እንድንመርጥ ያደርገናል፡፡ ከእናንተ በዕድሜ ከሚበልጡ ሴቶች ምክርን መጠየቅ ይጠቅማል፡፡ ሔዋን ሐጢአት ውስጥ ከመውደቅ አዳምን ወይም እግዚአብሔርን ጠይቃ ቢሆን የታሪኩ እውነት ሌላ ይሆን ነበር፡፡

<u>ሰባተኛ ሣምንት</u>

<u>ከመጽሐፍ ቅዱስ ሴቶች ሕይወት መማር</u>

<u>ዶርቃ፡- ሐዋ፡9፡36-43</u>

<u>ታሪክ፡- የአገልግሎት ሰው</u>

<u>መግቢያ፡- የዛሬው</u> ታሪካችን ስለ ዶርቃ ሕይወት ነው፡፡ የስሟ ትርጉም በተራራ ላይ የሚዘል ሚዳቋ የሚባል እንስሳ ማለት ነው፡፡ በመጀመሪያው ቤተክርስቲያን ዘመን የኖረች ሴት ናት፡፡ ስለእሷ ብርታት የሚያወራው ታሪክ በሐዋሪያት ሥራ ላይ ቀርቧል፡- ታሪኩን ተናገር፡፡

<u>የሚከተሉትንና ሌሎችን ጥያቄዎች በመጠየቅ ታሪኩን የበለጠ ግልጽ አድርግ፡፡</u>

1. ዶርቃ ምን ዓይነት ሴት ነበረች?
2. በእሷ ላይ ምን ሆነ?
3. በእሷ ከተማ አጠገብ የነበረው ማን ነበር?
4. የቤተክርስቲያን ሰዎች ምን አደረጉ?
5. ቀጥሎ ምን ሆነ?
6. መበለቶች ጴጥሮስን ምን አሳዩ?
7. ጴጥሮስ ምን አደረገ?
8. የዚህ ድንቅ ሥራ ውጤት ምን ነበር?

አሁን ታሪኩን አንብቡ፡፡ የተረሳ ነገር ካለ ተወያዩ፡፡

<u>የውይይት ጥያቄዎች</u>

1. ሴት ስለሆንሽ ከራስሽ ጋር ትታገዪያለሽ? አንዳንድ ጊዜ ‹‹ብዙ ጠቃሚ ሥራ ብሠራ›› ብለሽ ተመኝተሽ ታውቂያለሽ?
2. የዶርቃ ተግባራዊ አገልግሎት ምን እንደሆነ ግለጹ፡፡
3. ማህበረሰቡ ስለ እሷ ምን ይሰማው ነበር?
4. ዶርቃን እግዚአብሔር ለምን አዳናት? ይህ ስለእሷ ጠቃሚነትና አስፈላጊነት ምን ያስተምረናል? ይህ እግዚአብሔር ለድሆች ስላለው ርህራሄ ይህ ምን ያስተምረናል?
5. የዶርቃ ሕይወት አንተን እንዴት ያበረታታሃል?
6. ከዚህ ታሪክ የተነሣ በሕይወትህ እንዴት ለውጥ እንዲመጣ ትፈልጋለህ?

<u>አስተያየት፡-</u> ብዙ ሴቶች በቤተክርስቲያንና በቤታቸው ውስጥ ስላላቸው ሃላፊነት ሲቸገሩ ይታያሉ፡፡ እኛ ሁል ጊዜ መሪዎች ለመሆንና በውጪ የሚሠሩ ሥራዎች ለመሥራት እንፈልጋለን፡፡ ነገር ግን ባሎቻችን ወይም ወንድ መሪዎቻችን በቤት አካባቢ የሚሠሩ ሥራዎችን እንድንሠራ ይፈልጋሉ፡፡  የሚያገለግሉ ሴቶች በእግዚአብሔር ፊት ቦታ

እንዳላቸው ይህ ታሪክ ዛሬ ያስተምረናል። ኢየሱስ በምድር ላይ በነበረ ጊዜ አገልግሏል። ብዙ ስጦታዎችና እርዳታን በመስጠት እስከዛሬ ፍቅሩን እየገለጸ ነው። እኛም ፍቅራችንን ለሌሎች ማሳየት እንችላለን።

<u>ስምንተኛ ሣምንት</u>

<u>ከመጽሐፍ ቅዱስ ሴቶች ሕይወት መማር</u>

<u>አብጋል፦ 1ሳሙ፡25፡2-42</u>

<u>ታሪክ፦ የሰላም ተምሳሌትና መልካም ተጽዕኖ ያመጣች ሴት</u>

<u>መግቢያ</u>፦ ንጉሡ ሳዖል ዳዊትን ሊገድለው ሲለፈለገ ዳዊት በምድረ በዳ ይኖር ነበር። 600 (መቶ) ሰዎች ዳዊትን ተቀላቅለው እሥራኤላዊያንን ከፍልስጥኤማዊያን እጅ አዳኑአቸው። ስለዚህ ሕዝቡ ዳዊትን ያመሰግኑታል ብላችሁ ታስቡ ይሆናል። በዚህ ታሪክ ውስጥ አንድ ሰውዬና ሚስቱ ዳዊትን እንዴት እንደተቀበሉት እናያለን።

አሁን ታሪኩን ተናገር።

<u>የሚከተሉትንና ሌሎችን ጥያቄዎች በመጠየቅ ታሪኩን የበለጠ ግልጽ አድርግ።</u>

1. ናባልና ሰዎቹ ምን ያደርጉ ነበር?
2. ዳዊት ከእሱ ምን ፈለገ? ናባል ለዳዊት ሰዎች ምን አለ? ዳዊት ምን ለማድረግ ወሰነ? ቀጥሎ ምን ሆነ?
3. አብጋል ዳዊትን ምን አለችው? ዳዊት እሷን ምን አላት?
4. ናባል በዚያን ጊዜ ምን ያደርግ ነበር?
5. አብጋል የሆነውን ነገር ለባለቤቷ መቼ ነገረችው? ናባል ምን ሆነ?

ታሪኩን አንብቡ።

<u>የውይይት ጥያቄዎች</u>

1. በዚህ ታሪክ ውስጥ ናባል፣ዳዊትና አብጋል ምን ዓይነት ሰዎች እንደሆኑ ግለጹ።
2. ዳዊት በተቆጣ ጊዜ አብጋል እንዴት አናገረችው እያንዳንዱን ክፍል ተመለከቱና ተወያዩ።
3. ለችግር መፍተሔ ስለማምጣትና ሰላምን ስለመፍጠር ከአብጋል ሕይወት ምን እንማራለን?
4. አንድ ችግር ሲፈጠር ችግሩን ለማቃለል ምቹ ጊዜ ስለማግኘት ከዚህ ምን እንማራለን?
5. ዳዊት ለምን አብጋልን ለማግባት ፈለገ?
6. አንድ ችግር ሲፈጠር ከእነዚህ ከሦስቱ ሰዎች (አብጋል፣ዳዊትና ናባል) የትኛውን ትመስላለህ?
7. እግዚአብሔር ምን ያስተምርሃል?

<u>አስተያየት</u>፦ አብጋል በአገሯ ባሕል መሠረት ዋጋ የሌላት ስትሆን በባለቤቷም ዘንድ ዋጋ ያጣች ሴት ነበረች። ነገር ግን አቅሟ የቻለውን ሁሉ አደረገች። እሷ ለዳዊት የሰጠችው ምክር ብዙ ሰዎችን ሕይወት አዳነ። እኛ ሁላችን ጥበብን ማግኘት እንችላለን። ያዕቆ፡1፡5 ላይ እኛ ሁላችን ጥበብን ከእግዚአብሔር መለመን እንደምንችል

ይናገራል፡፡ ችግር በሚመጣበት ጊዜ አማራጮች አሉን፡፡ ችግር በሚመጣበት ጊዜ ችግሩን ማስወገድ እንችላለን፡፡ ምክርን የማንሰማ ከሆነ ችግሩን ልናስወግድ እንችልም፡፡ ያኔ የእግዚአብሔር ፍርድ ይመጣብናል ማለት ነው፡፡ በቤታችንና በሕብረተሰባችን ሰላምን የምናመጣ ሴቶች ልንሆን እንችላለን፡፡

<u>ዘጠነኛ ሣምንት</u>

<u>ከመጽሐፍ ቅዱስ ሴቶች ሕይወት መማር</u>

<u>አጋር፦ ዘፍ፡16</u>

<u>ታሪክ፦ መቸገርህን እግዚአብሔር ያያል፡</u>

<u>መግቢያ</u>፦ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለሚገኙ ሴቶች እየተማርን ነው፡፡ በብሉይ ኪዳን የሚትገኝ አንዲት ሴት ከሕይወቷ የምንማረው ነገር እንደለሌ እናስባለን፡፡ ምክንያቱም እሷ ግብፃዊት እንጂ አይሁዳዊት አይደለችምና፡፡ አብርሃምና ሣራ በራሃብ ምክንያት ወደ ግብፅ ወረዱ፡፡ የፈርኦን ባለሥልጣናት የሣራን ውበት አደነቁና ወደ ቤተመንግሥት አስገቧት፡፡ አብርሃምንም በደህና ተቀበሉት፦ከብቶችን፣በጎችን፣አህዮችንና አሽከሮችንም ሰጡት፡፡ ከአሽከሮቹ አንዷ አጋር ትባላለች፡፡ የአጋር ታሪክ ከዚህ ቀጥሎ ቀርቧል፡፡ ከዘፍ፡16 ታሪኩን ተናገሩ፡፡

<u>የሚከተሉትንና ሌሎችን ጥያቄዎች በመጠየቅ ታሪኩን የበለጠ ግልጽ አድርግ</u>፡፡ በተቻለ መጠን መልሶቹን ቀለል ማድረግ አለብህ፡፡ ልብ በሉ ይህ ታሪኩን በቃል የምንናገርበት ጊዜ እንጂ የውይይት ጊዜ ገና አልደረሰም፡፡ ለዚህ ሣምንት የሚሆኑ የጥያቄ ዓይነቶች፦ ማን፣ምን፣እንዴት፣ዬት፣የሚሉት ናቸው፡፡

1. የሣራ ችግር ምን ነበር? ችግሩ በምን ዓይነት መንገድ እንዲቃለል ፈለገች?
2. ቀጥሎ ምን ሆነ? ሣራ አሁን ምን ተሰማት? ሣራ አጋርን ምን እንድታደርጋት ነው አብርሃም የነገራት? ቀጥሎ ምን ሆነ?
3. መልአኩ አጋርን ምን አላት? ምን የሚል ተስፋ ሰጣት? እሷ ለእግዚአብሔር የሰጠችው ስም ማን ነበር? ትርጉሙ ምንድነው? ለልጇ የሰጠችውስ ስም ምን ነበር?

ታሪኩን አንብቡ፡፡ ታሪኩን ስንናገር የረሳነው ነገር አለ?

<u>የውይይት ጥያቄዎች</u>

1. ስለ አጋር ምን እንማራለን?
2. ስለ ሣራ ምን እንማራለን? ሣራ ለምን ተቆጣች?
3. ለአጋር የነበራት ምርጫ ምን ነበር?
4. በታሪኩ ውስጥ ካሉ ሰዎች የትኛውን ትመስላለህ? አጋርን ወይስ ሣራን? ለምን?
5. ሰው ጠልቶህ ያውቃል? ያንን ሰው ስትረዳው በራሱ ጊዜ አልፈልግህም ብሎህ ያውቃል? ያኔ ምን አደረክ?
6. ስለ እግዚአብሔር ምን እንማራለን?
7. እግዚአብሔር እርሱን የሚፈልጉትን አይጥልም:: ሰው ቢጎዳን ምን ማድረግ አለብን?
8. ጻድቅ ፈራጅ እግዚአብሔር አንድ ቀን ፍርዱን ያመጣል፡፡ 2ተሰ፡1፡5-10 አንብቡ፡፡ ባንተ ላይ ለሚደርሰው ግፍ የመጨረሻው ውጤት ምንድነው?
9. የእግዚአብሔርን ስም ማወቅ እንዴት ይረዳናል?

10. ችግሮች ሲመጡ ምን ታደርጋለህ? ችግር ሲመጣ ትሸሻለህ? ወይስ ትደበቃለህ? ወይስ ወደ እግዚአብሔር ፊትህን አዙረህ ምላሽና ጥንካሬ እንዲሰጥህ ትለምነዋለህ?
11. ከዚህ ታሪክ የተነሣ በዚህ ሣምንት ምን የተለየ ነገር ታደርጋለህ?

<u>አስተያየት፡-</u> በሰው ዘንድ የተጠሉትን፣የተገፉትንና ያልተወደዱትን ሴቶች አስቡ፡፡ ለእነዚህ ሰዎችና ለእኛም የምሥራች ይሆን ዘንድ እግዚአብሔር ሁሉን እንደሚያይና እንደሚወደን እንዲሁም አንድ ቀን በጽድቅ እንደሚፈርድ መረዳት አለብን፡፡ ምናልባት ሁኔታዎቻችን እንደነበሩ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን ከእግዚአብሔር ጋር ባለን ግንኙነት ሰላም ሊኖረን ይችላል፡፡

<u>አሥረኛ ሣምንት</u>
<u>ከመጽሐፍ ቅዱስ ሴቶች ሕይወት መማር</u>
<u>ሣራ፡- ዘፍ፡17፡15-22፣18፡1-15፣21፡1-6</u>
<u>ታሪክ፡- የእግዚአብሔርን ቃል ማመን</u>
<u>መግቢያ</u>፡- ሣራ የአህዛብ እናትና የኢየሱስ የዘር ግንድ ነበረች፡፡ ነገር ግን ልጅ እስኪታገኝ 90 ዓመት ቆየች፡፡ አንድን ነገር በትዕግስት መጠበቅ ለእኛ በጣም ከባድ ነው፡፡ በተለይም አንድ በጣም ልናገኘው የምንጓጓለት ነገር ከሆነ መጠበቁ የበለጠውን ይከብዳል፡፡ የሣራ ታሪክ ከዚህ ቀጥሎ ቀርቧል፡
ታሪኩን ተናገር፡፡
<u>ታሪኩን የበለጠ ግልጽ ለማድረግ የተለያዩ ጥያቄዎችን ጠይቁ፡፡</u>
ታሪኩን አንብብ፡፡
<u>የውይይት ጥያቄዎች</u>

1. አብርሃምና ሣራ ለምን ሣቁ? ስለ አብርሃምና ሣራ እምነት ምን እንማራለን?
2. እግዚአብሔር ቃል ኪዳን የገባላቸውን ልጅ እስኪሰጥ ድረስ ለምን 25 ዓመታትን እንዲጠብቁ አደረገ?
3. ስለ እግዚአብሔር ምን እንማራለን? እግዚአብሔር ለአብርሃምና ሣራ ሣቅ ምን ምላሽ ሰጠ?
4. ከሣራ ሕይወት የምንማረው ምንድነው? ዕብ፡11፡11 አንብቡ፡፡
5. አንድን ነገር በእምነት ለመጠበቅ የተቸገርክበት ጊዜ አለ?
6. በእግዚአብሔር ላይ ጠንካራ እምነት እንድኖረን እንዴት ማድረግ እንችላለን?
7. ከሣራና ከይሣቅ ታሪክ የተነሣ በዚህ ሣምንት ምን የተለየ ነገር ታደርጋለህ?

<u>አስተያየት፡-</u> እግዚአብሔር እምነት እንዲኖረን ይፈልጋል፡፡ በእሱ ላይ የምንጠራጠር ከሆነ እሱን ደስ ልናሰኝ አንችልም፡፡ በእሱ ላይ እምነት እንዲኖረን እግዚአብሔር በመከራ ውስጥ ሊያስተምረን ይፈልጋል፡፡ እምነታችን በእግዚአብሔርና በቃሉ ላይ መሆን አለበት፡፡ እግዚአብሔር አይዋሽም፡፡ አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር ከአቅማችን በላይ የሆነ ነገር እንድናደርግ ሊጠይቀን ይችላል፡፡ ያ የእምነት ፈተና ነው፡፡ በዚህ ጊዜ የራሳችንን ውሳኔ እንድናደርግ እንገደዳለን፡፡ ውሳኔያችን በእግዚአብሔር ማመንና እርሱ ሁሉን ቻይ እንደሆነ ማመን ሊሆን ይገባል፡፡ ስለዚህ እምነታችንን በእርሱ ላይ እናድርግ፤እርሱንም እንታዘዝ፡፡

*አሥራ አንደኛ ሣምንት*

*ከመጽሐፍ ቅዱስ ሴቶች ሕይወት መማር*

ርብቃ፡- ዘፍ፡24፡1-30፣48-67

*ታሪክ፡- በእግዚአብሔር መመራት*

*መግቢያ፡-* የዛሬው ታሪክ የሚጀምረው በአብርሃም ማርጀትና በሚስቱ ሣራ መሞት ነው፡፡ አብርሃም ልጁ ይሣቅ አማኝ ሚስት እንዲኖረው በጣም ይፈልግ ነበር፡፡ ይሣቅ እግዚአብሔር የተስፋ ቃሉን ሲፈጽምበት የመረጠው ልጅ እንደሆነ አብርሃም ያውቅ ነበር፡፡ አገልጋዩ ከዘመዶቹ ዘንድ ሄዶ ለይሣቅ ሚስት እንዲፈልግለት አብርሃም አዘዘው፡፡ ታሪኩ ከእግዚአብሔር ቃል እንደሚከተለው ቀርቧል፡-

*ታሪኩን ተናገር፡፡ ታሪኩን ስትናገሩ ‹‹ምንም ሣይቀር መናገር አለብኝ›› ብላችሁ አትጨነቁ፡፡ ልብ በሉ ታሪኩን መናገር እንጂ መሸምደድ የለባችሁም፡፡*

*ታሪኩን የበለጠ ግልጽ ለማድረግ ጥያቄዎችን ጠይቅ፡፡*

*ታሪኩን አንብብ፡፡ የቀረ ወይም የተጨመረ ነገር ካለ የቡድኑን አባላት ጠይቅ፡፡*

*የውይይት ጥያቄዎች*

1. ስለ እግዚአብሔር ምን እንማራለን?
2. ስለ ርብቃ ምን እንማራለን?
3. ርብቃ አሥሩን ግመሎች ለምን ውሃ አጠጣች?
4. ማንኛውንም ነገር በማንኛውም ቦታና ጊዜ ለማድረግ ፈቃደኛ ስለመሆን ከርብቃ ሕይወት እንዴት እናያለን?
5. ለርብቃ መሄዷ ቀላል የሆነ ይመስልሃል? እሷ ለምን ሄደች? ለእግዚአብሔር ስለታዘዘች በምን መንገድ ነው እግዚአብሔር የባረካት?
6. ለእግዚአብሔር ራስን ስለመስጠት ምን እንማራለን?
7. እግዚአብሔር በግልህ ዛሬ ምን ያስተምርሃል?
8. ከዚህ ታሪክ የተነሣ በዚህ ሣምንት ምን የተለየ ነገር ታደርጋለህ?

ሮሜ፡8፡28-30 አንብብ፡፡ ይህንን ክፍል በቃል ለማጥናት ሞክሩ፡፡

*አስተያየት፡-* እኛ ክርስቲያን ሴቶች የክርስቶስን መልክ ለመያዝ መንፈሳዊ ጉዞ እየተጓዝን ነን፡፡ ሮሜ፡8፡28-30 ላይ ‹‹እግዚአብሔርን ለሚወዱት እንደ ሃሳቡም ለተጠሩት ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለን›› ይላል፡፡ ስለዚህ ከአቅማችን በላይ የሆነ ነገር እንድናደርግ እግዚአብሔር ቢያዘን በእርሱ ታምነን ማድረግ አለብን፡፡ እግዚአብሔር ዓላማው እኔን መለወጥ ነው፡፡ ነገር ግን ለፈቃዱ ራሴን መስጠት፣እርሱን ማመንና እርሱን መከተል አለብኝ፡፡ ርብቃ ማንኛውን ነገር በማንኛውም ቦታና ጊዜ ለማድረግ ፈቃደኛ ነበረች፡፡ እርሷ ራሷን ለእግዚአብሔር ፈቃድ አሳልፋ ስለሰጠች እግዚአብሔር ባረካት፡፡

_አሥራ ሁለተኛ ሣምንት_
_ከመጽሐፍ ቅዱስ ሴቶች ሕይወት መማር_
<u>ርብቃ፡- ዘፍ፡25፡28 እና 27፡1-46</u>
_ታሪክ፡- እግዚአብሔር ፈቃዱን እንዲያደርግ መታመን_
_መግቢያ_፡- ባለፈው ሣምንት ስለወጣቷ ሴት ስለ ርብቃ ተምረን ነበር፡፡ እርሷ እግዚአብሔርን የምትሰማና የምትታዘዝ ሴት ነበረች፡፡ በመጨረሻም እግዚአብሔር ባረካት፤ያዕቆብንም አገባች፡፡ ርብቃ ነፍሰ ጡር በነበረችበት ጊዜ በሆዷ ውስጥ ያሉ መንታ ልጆች ለምን እርስ በርሳቸው እንደሚገፋፉ እግዚአብሔርን ጠየቀች፡፡ ጌታም፡- ‹‹ሁለት ወገኖች በሆድሽ አሉ፤ አንዱ ከአንዱ ይበረታል፤ታላቁም ለታናሹ ይገዛል፤›› አላት፡፡
ልጆቹ ካደጉ በኋላ ርብቃ ያዕቆብ የተባለውን ታናሹን ልጇን ወደደችው፡፡ ታሪኩ ከእግዚአብሔር ቃል እንደሚከተለው ቀርቧል፡-
መጽሐፍ ቅዱስ ዘግታችሁ ታሪኩን ተናገሩ፡፡
ታሪኩን ግልጽ ለማድረግ ጥያቄዎችን ጠይቅ፡፡
አሁን ታሪኩን አንብቡ፡፡
_የውይይት ጥያቄዎች_

1. ስለቤተሰብ ምን እንማራለን?
2. ርብቃ ባሏን ለምን አታለለችው?
3. ስለመገዛት ምን እንማራለን?
4. ስለሴቶች ምን እንማራለን?
5. ስለግል ሕይወትህ ምን ትማራለህ?
6. ከዚህ ታሪክ የተነሣ በዚህ ሣምንት ምን የተለየ ነገር ታደርጋለህ?

_አስተያየት_፡- አንዳንድ ጊዜ በራስህ ፈቃድ ተነሳስተህ ነገሮችን አድርገህ ለማየት ትፈልጋለህ? የምትፈልገውን ነገር ለማግኘት ትዋሻለህ ወይም ታታልላለህ? ርብቃ ያደረገችው ይህንን ነው፡፡ እርሷ ይህንን ያደረገችው ያዕቆብ የአባቱን በረከት እንዲያገኝ በማድረግ የእግዚአብሔርን ዕቅድ ለማሳካት ፈልጋ ሊሆን ይችላል፡፡ ይህ ትክክል ነው በማለት ድርጊቷን ፈጸመች፡፡ የምትሰራው ሥራ ሌላውን ስለማይጎዳና የእግዚአብሔር ሃሳብ እንደሆነ ስለምታስብ ትክክል ነው ብለህ ትሰራለህ? ለአንድ ቀን ብቻ ሣይሆን በሕይወት ዘመንህ ሁሉ ለእግዚአብሔር መገዛት ያስፈልግሃል፡፡

_አሥራ ሦስተኛ ሣምንት_
_ከመጽሐፍ ቅዱስ ሴቶች ሕይወት መማር_
_የሳምሶን እናት፡- መሳፍ፡13_
_ታሪክ፡- ፍቅርና አክብሮት_
_መግቢያ_፡- በመሳፍንት ዘመን የእሥራኤል ሕዝብ ብዙ ጊዜ በእግዚአብሔር ላይ አመጹ፡፡ በመከራ ላይ ሆነው ወደ እግዚአብሔር ጮኹ፡፡ እግዚአብሔር አዲስ መስፍን (ዳኛ) ወይም መሪ ላከላቸው፡፡ የዛሬው ታሪካችን የሚያተኩረው ልክ እንደ እናንተ ባለች ሴት ሕይወት ላይ ነው፡፡ ስሟን እንኳ እኛ አናውቅም፤ነገር ግን እግዚአብሔር አከበራት፡፡ ታሪኩ ከመሳፍ፡13 እንደሚከተለው ቀርቧል፡-

ታሪኩን ተናገር። ታሪኩን የበለጠ ግልጽ ለማድረግ ጥያቄዎችን ጠይቅ። መልሶቹን ቀለል ለማድረግ ሞክር። በዚያ በእስራኤል ምድር የነበረው ችግር ምን ነበር? መልዓኩ ለሴቷ ምን ነገራት? እሷ ምን አደረገች? ባሏ ምን አደረገ? መልዓኩ እንደገና ለማን ተገለጠ? ማኑሄ ለመልዓኩ ምን ማድረግ ፈለገ? ቀጥሎ ምን ሆነ?
አሁን ታሪኩን አንብብ።

<u>የውይይጥ ጥያቄዎች</u>

1. መልዓኩ ለምን ቀድሞ ለሴቷ የተገለጠ ይመስልሃል? እግዚአብሔር ለልጇ የገባው ተስፋ ቃል ምን ነበር? በእግዚአብሔር ዕቅድ ውስጥ የእሷ ድርሻ ምን ነበር?
2. ሴቷ ከባሏ ጋር ስላላት ግንኙነት የምንማረው ምንድነው?
3. ማኑሄ ምን ዓይነት ሰው፣አባት ወይም ባል ነበር?
4. ማኑሄ ለምን መልዓኩ ተመልሶ እንዲመጣ ጠየቀው?
5. በጋብቻ ውስጥ ስላለው መከባበርና መዋደድ ምን እንማራለን?
6. ስለ እግዚአብሔር ምን እንማራለን?
7. ከዚህ ታሪክ እግዚአብሔር ምን ያስተምርሃል?
8. ከዚህ ታሪክ የተነሳ ሕይወትህ እንዴት እንዲለወጥ ትፈልጋለህ?

<u>አስተያየት፡-</u> ይህችን ሴት እግዚአብሔር በመልዓኩ በኩል ማክበሩ የሚገርም ነው። መልዓኩ ቀድሞ ለእሷ ተናገረ። መልዓኩ በተለያየ ጊዜ ተገልጦ የጎበኛትን ጉብኝት ለባሏ በመናገር ለእርሱ ያላትን አክብሮት አሳየችው። ባሏ ደግሞ እርሷን በመስማትና ምክሯን በመቀበል ለእሷ ያለውን አክብሮት  አሳያት። ፍቅርና አክብሮት በሁሉም ግንኙነቶች በጣም አስፈላጊ ሲሆኑ በተለይ በጋብቻ ሕይወት በጣም የሚያስፈልጉ ነገሮች ናቸው። ማኑሄ በቤተሰብ አምልኮና ፀሎት መንፈሳዊ መሪና መልካም አባት ለመሆን ጥበብን ከእግዚአብሔር የሚሻ ሰው ነበር። ሚስቱ የእርሱን መሪነት ታከብረዋለች። እና እግዚአብሔር ይህችን ሴት ልዮ ልጅ በመስጠትና በመልዓኩ እንድትጎበኝ በማድረግ አከበራት።

<u>አሥራ አራተኛ ሣምንት</u>

<u>ከመጽሐፍ ቅዱስ ሴቶች ሕይወት መማር</u>

<u>ሩትና ኑኃሚን</u>

<u>መግቢያ፡-</u> ለሚቀጥሉት አራት ሣምንታት ስለ ሩትና ኑኃሚን እናጠናለን። ይህ ለሁሉም ሴቶች በረከት ይሆን ዘንድ ፀሎቴ ነው። ከእነዚህ ሁለቱ ሴቶች ሕይወት ብዙ ተግባራዊ ነገሮችን መማር እንችላለን። መጽሐፉን በምታጠኑበት ጊዜ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን አምስቱን ነጥቦች አስቡ። ክፍሎቹን በምታነበቡበት ጊዜ እነዚህን ነጥቦች የሚያሳዩ ቦታዎች ስትደርሱ በነጥቦቹ ፊት ለፊት ምዕራፎቹንና ቁጥሮቹን ጻፉ።
ነጥቦች፡-

- ታማኝነት
- ቸርነት
- ትጋት

- ከለላ
- በረከት

<u>ክፍል አንድ</u>

*<u>መግቢያ፡-</u> የሩት ታሪክ በመሳፍንት ዘመን የሆነ ታሪክ ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ሁሉም ሰው በዓይኑ ፊት መልካም የመሰለውን ያደርግ ነበር፡፡ ሕዝቡ እግዚአብሔርን ያልተከተሉበትና በእግዚአብሔር ላይ ያመፁበት ጊዜ ነበር፡፡ ነገር ግን በዚህ ክፉ ጊዜ ለእግዚአብሔርና ለራሳቸው ታማኝ የሆኑ ሁለት ቆንጆ ሴቶችን በዚህ ታርክ እናገኛለን፡፡*

*ሩት፡1 ላይ ያለውን ታሪክ ተናገር፡፡*

1. *የሚከተሉትን የምልከታ ጥያቄዎች በመጠየቅ ታሪኩን እንደገና ግልጽ አድርገህ ተናገር፡፡*
   *ሀ. አቤሜሌክና ቤተሰቦቹ ወደ ሞዓብ ምድር የሄዱበት ምክንያት ምንድነው?*
   *ለ. ቤተሰቡን በሞዓብ ምድር ምን አጋጠማቸው?*
   *ሐ. ኑኃሚን ወደ አገሯ ይሁዳ ምድር ልትመለስ የወሰነችው ለምንድነው?*
   *መ. ኑኃሚን ለምራቶቿ(የሁለቱ ወንድ ልጆቿ ሚስቶች) ምን አለች?*
   *ሠ. ቀጥሎ ምን ሆነ?*
   *ረ. ሩት ምን ለማድረግ ወሰነች? ለኑኃሚን ምን አለች?*
   *ሰ. ወደ ቤተለሔም ሲደርሱ ምን ሆነ?*
   *ረ. ጊዜው በዓመቱ በየትኛው ወር ነበር?*

*ታሪኩን አንብብ፡፡*

*<u>የውይይት ጥያቄዎች</u>*

1. *ሩት ሞዓባዊት ስለነበረች በአይሁድ ዘንድ በጠላትነት የተፈረጀች ሴት ነበረች፡፡ ሩት ለኑኃሚን ምን ያህል ታማኝ እንደነበረች ተወያዩ፡፡ ታማኝ ስለመሆን ከሕይወታችን ምን እንማራለን? ስለ እግዚአብሔር ምን እንማራለን?*
2. *ኑኃሚን ምራቶቿን እንዴት አናገረቻቸው? ለከተማዋ ሰዎች ምን አለች? ስለኑኃሚን ምን እንማራለን?*
3. *ሩት በእግዚአብሔር ላይ የነበራት እምነት ምን ያህል እንደሆነ ተወያዩ፡፡ ኑኃሚን እምነቷን ለሩት እንዴት አሳየቻት? ኑኃሚን በሀዘኗና በደስታዋ ጊዜ ለሩት ታማኝ ነበረች?*
4. *ሩትና ኑኃሚን ልዩነታቸው ምንድነው? ሩትና ኑኃሚን እንዴት ጥሩ ጓደኞሞች ሆኑ? ግኑኙነታቸውን ያጠነከረው ምንድነው? ያ ስለግንኙነት ምን ያስተምራችኋል?*
5. *እምነት ሲጎድልባችሁ ከሌሎች ጋር ትነጋገራላችሁ? ይህ ከሌሎች ጋር የጠለቀ ግንኙነት እንድታደርጉ ያደርጋችኋል?*

*<u>ክፍል ሁለት</u>*

*<u>ሩትና ኑኃሚን፡- ሩት፡2</u>*

*<u>መግቢያ፡</u>- እግዚአብሔር እርሱን እንዲያውቁት አይሁድን መረጠ፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ከአይሁድ ቤተሰብ ነው የተወለደው፡፡ በእርሱ በኩል ዓለሙ በሙሉ እግዚአብሔርን እንዲያውቅ ነው፡፡ የሩት መጽሐፍ እግዚአብሔርን ለሚያመልኩ ሰዎች እግዚአብሔር ምን ያህል ልብ እንደነበረው ያሳያል፡፡ ሩት አይሁድ አይደለችም፡፡ ነገር ግን ከእምነቷ የተነሣ እግዚአብሔር ባረካት፡፡ የሚቀጥለው ታሪኳ ከዚህ ቀጥሎ ቀርቧል፡*

*ሩት፡2 ላይ ያለውን ታሪክ ተናገሩ፡፡ የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ታሪኩን እንደገና ተናገሩ፡፡*

1. *የኑኃሚን ዘመድ ማን ነበር?*

2. ኑኃሚንና ሩት ሁለቱም መበለትና ድሃ ነበሩ፡፡ ሩት ምን እንድታደርግ ነው ኑኃሚን የነገረቻት?
3. ቦኤዝ አዲሷን ሠራተኛ አያት፡፡ ካያት በኋላ ምን አደረገ? ምን በማድረግ ነው መልካምነቱን ያሳያት?
4. ቦኤዝ ለምንድነው ለሩት መልካም ያደረገላት?
5. ኑኃሚን ለቦኤዝ መልካምነት ምን ምላሽ ሰጠች?

አሁን ምዕራፉን አንብብ፡፡

<u>የውይይት ጥያቄዎች</u>

1. ዛሬ ስለመልካምነትና ለሌላው ከለላ ስለመሆን እንማራለን፡፡ በዚህ ታሪክ ውስጥ በሰዎች መካከል መልካምነትና ከለላ የታየባቸውን ብዙ መንገዶች ተወያዩ፡፡
2. በዚህ ታሪክ ውስጥ ስለ ሩት ምን እንማራለን? እሷ ምን ዓይነት ሰው ነበረች? ይህ እንዴት መልካም ምስክርነት እንዲኖራት ያደርጋል?
3. እግዚአብሔር እንዴት ኑኃሚንና ሩትን ከረሃብ ታደጋቸው? ሩት የመጀመሪያውን እርምጃ በመውሰድ ተነስታ መሄዷ ለምን ይጠቅማል? ከዚህ ምን ትማራላችሁ?
4. ቦኤዝ ባህሉ ወይም ወጉ ከሚያዝዘው ውጭ ከተጠበቀው በላይ እንዴት ሰጣት? ከቦኤዝ መልካምነትና ከለላ ከማድረጉ ምን እንማራለን?

<u>አሥራ አምስተኛ ሣምንት፡ ኑኃሚንና ሩት፡ ሩት፡3</u>

<u>መግቢያ</u>፦ ኑኃሚንና ሩት መበለት ከመሆናቸው የተነሣ አስቸጋሪ ጊዜአቶችን አሳልፈዋል፡፡ አንድ የሚቀርባቸው ሰው ካልረዳቸው በስተቀር የወደፊት ተስፋቸው የመነመነ ይሆን ነበር፡፡ ነገር ግን በእነሱ ሕይወት እግዚአብሔር ዓላማ ነበረው፡፡ በእስራኤል ባሕል መሠረት አሽከሩ ከጌታው እግር ሥር ይተኛ ነበር፡፡ ይህ የሚደረገው ከጌታው ከሌላ ለማግኘት ነበር፡፡ ቀጣዩ ታሪክ ከዚህ በታች ቀርቧል፦

ከምዕራፍ 3 ታሪኩን ተናገሩ፡፡

<u>የሚከተሉትንና ሌሎችን ጥያቄዎች በመጠየቅ ታሪኩን የበለጠ ግልጽ አድርጉ፡፡</u>

1. ኑኃሚን ለሩት ስለ ቦኤዝ ምን ነገረች? በዚያ ሌሊት ሩት ምን እንድታደርግ ነው ኑኃሚን የነገረቻት?
2. ሩት ምን አደረገች?
3. ቦኤዝ ምን ምላሽ ሰጣት?
4. ሩት ቀጥላ ምን አደረገች? በሚቀጥለው ቀን ጧት ምን ሆነ?

ምዕራፍ፡3 አሁን አንብቡ፡፡

<u>የውይይት ጥያቄዎች</u>

1. ሩትና ቦኤዝ እንዴት ታማኝነትን አሳዩ? የአኗኗር ሥርዓታቸው የሚለካው በምንድነው?
2. ሩት የኑኃሚንን ምክር ለምን ተከተለች? የአገሩን ባህል ለማያውቅ ሰው ሁሉም ነገር እንግዳ ይሆን ነበር፡፡
3. ምክር ሊለግስልኝ ይችላል ብለህ የምታስበው በዕድሜ ጠና ያለ ሰው ታውቃለህ?
4. ቦኤዝ እንደቅርብ ዘመድ ለሩት ባል እንዲፈልግላት ኑኃሚን ጠየቀችው፡፡ ቦኤዝ ምን ዓይነት ሰው ነበር? ስለ ቦኤዝ ምን እንማራለን? ቃል የገባኸውን ነገር ሁሌ ትፈጽማለህ?

5. ስለ ሕይወታችን ዛሬ ምን እንማራለን?

<u>*አሥራ ስድስተኛ ሣምንት፡ ሩትና ኑኃሚን፡ ሩት፡4*</u>

<u>*መግቢያ*</u>፡- የከተማው በር ብዙ ሥራ የሚሠራበት ቦታ ነበር፡፡ በዋናው በር ካልሆነ በስተቀር ማንም ወደ ውጪ መውጣት አይችልም፡፡ እንዲሁም የከተማው ንግድ የሚከናወንበት በዚህ ቦታ ነበር፡፡ ስለዚህ የታሪኩ ሁለተኛው ክፍል ሩት ቦኤዝን ለእርዳታ በጠየቀችበት ሁለተኛው ቀን ይጀምራል፡፡

ከምዕ፡4 ታሪኩን ተናገሩ፡፡

<u>የሚከተሉትንና ሌሎችን ጥያቄዎች በመጠየቅ ታሪኩን የበለጠ ግልጽ አድርጉ፡፡</u>

1. ቦኤዝ ማንን ለማየት ነው ወደ በሩ የሄደው? ለምን?
2. ቦኤዝ ለዘመዱ ታሪኩን እንዴት ተናገረ? ከዚህ የምንማረው አዲስ ነገር ምንድነው?
3. የቦኤዝ ዘመድ መሬቱን ለመግዛት ያልፈለገው ለምንድነው? ይህ ቦኤዝን እንዴት ረዳው?
4. ቦኤዝ በበሩ ላሉ ሰዎች ምን ዓይነት ማስታወቂያ ተናገረ? በበሩ የነበሩ ሽማግሌዎች ምን ምላሽ ሰጡ?
5. የታሪኩ መጨረሻ ምን ነበር? ማን ተወለደ? በቦኤዝና በሩት የዘር ሀረግ ውስጥ የነበረው ታላቁ ሰው ማን ነበር?

ታሪኩን አንብቡ፡፡

<u>የውይይት ጥያቄዎች</u>

1. ቦኤዝ ወደ ዘመዱ በመሄዱ ታማኝ መሆኑን እንዴት እናያለን?
2. ኑኃሚን አስቸጋሪ ጊዜአቶችን ቢታሳልፍም እግዚአብሔር የሰጣት ታላቅ በረከት ምንድነው? ከውጫዊ በረከት ባሻገር ያሉ ሌሎች በረከቶችን አስቡ፡፡ ከሁሉ የሚልቁ በረከቶች ምንድናቸው?
3. ስለ እግዚአብሔር ምን እንማራለን?
4. ሩት ታማኝ ሆና ስለታዘዘች በሕይወቷ ትልቅ ዓላማ ነበር፡፡ ከዚህም የተነሣ የንጉሡ ዳዊት አያት ሆነች፡፡ መስሑ ኢየሱስ የዘር ሀረጉ ከዳዊት ነበረ፡፡ እሷ ከኑኃሚን ጋር ለመኖር ስትወስን ሕይወቷ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ አላወቀችም፡፡ ከዚህ ምን እንማራለን?
5. እግዚአብሔር ዛሬ ምን ያስተምራችኋል?

<u>*አሥራ ሰባተኛ ሣምንት*</u>

<u>*ከመጽሐፍ ቅዱስ ሴቶች ሕይወት መማር*</u>

<u>*መግደላዊት ማሪያም፡- ዮሐ፡20*</u>

ታሪክ፡- እግዚአብሔርን ለመውደድና ለማገልገል ከአጋንንት እሥራት ነፃ የወጣች ሴት

መግቢያ፡- መግደላዊት ማሪያም እርዳታ ፈልጋ ወደ ኢየሱስ የመጣች ሴት ነበረች፡፡ ከዚያም ኢየሱስ ሰባት አጋንንት ከእሷ በማውጣት ነፃ አወጣት፡፡ ከዚያም ኢየሱስ በሄደበት ሁሉ ተከተለችው፡፡ ታሪኩ ከዚህ ቀጥሎ ቀርቧል፡

ከማቴ፡27፡55-61 እና ዮሐ፡20 ታሪኩን ተናገሩ፡፡

የሚከተሉትንና ሌሎችን ጥያቄዎች በመጠየቅ ታሪኩን የበለጠ ግልጽ አድርግ፡፡

1. የኢየሱስን አካል ወስዶ የቀበረው ማን ነበር? መግደላዊት ማሪያምና ሌሎቹ ሴቶች የት ነበሩ? ሰዎቹ ኢየሱስን ምን ሲያደርጉ ነው እነዚህ ሴቶች ያዩት?
2. ማሪያም መቼ ወደ መቃብሩ ተመልሳ መጣች? ምን አየች? ምንስ አደረገች?
3. ለደቀመዛሙርቱ ሄዳ ምን አለች?
4. ጴጥሮስና ዮሐንስ ምን አደረጉ? ከዚያ በኋላ ምን አዩ?
5. ማሪያም የት ነበረች? ምን ታደርግ ነበር?
6. ቀጥሎ ምን ሆነ? መላእክቱ ማሪያምን ምን ጠየቋት?
7. ቀጥሎ ማን ተገለጠ? ኢየሱስ ማሪያምን ምን ብሎ ጠየቃት?
8. እሷ ምን አለችው?
9. ኢየሱስ ለመግደላዊት ማሪያም ምን ነገራት? እሷ ምን እንድታደርግ ፈለገ?

አሁን ታሪኩን አንብብ፡፡

የውይይት ጥያቄዎች

1. የኢየሱስን ስቅለት ስላዩ ሴቶች የምናውቀው እውነት ምንድነው?
2. በእግዚአብሔር ቃል መሠረት ስለመግደላዊት ማሪያም ተናገሩ፡፡ ምን ዓይነት ባሕሪ ነበራት? ባሕሪዋን የሚያንፀባርቅ ሥራ የሠራችው ምን ነበር?
3. መግደላዊት ማሪያም ለምን ኢየሱስን ተከተለች? እግዚአብሔርን ስለማመስገንና ለእርሱ ራስን ስለመስጠት ምን እንማራለን?
4. ማሪያም ከኢየሱስ ጋር ለመጣበቅ ወሰነች፡፡ ኢየሱስ ከእሷና ከሌሎች ጋር ስላለው ግንኙነቱ ሊያስተምራት የፈለገው ምንድነው?
5. ይቅርታ ስለማድረግ የተማራችሁት ነገር ምንድነው? እግዚአብሔርን ለማገልገል ነፃ ወጥተሻል? ገላ፡5፡13-14 አንብቡ፡፡ ምን ተምራችኋል?

አስተያየት፡- መግደላዊት ማሪያም ከሰይጣን እሥራት ነፃ የወጣች ሴት ነበረች፡፡ በኋላም ራሷን ለኢየሱስ ሰጠች፡፡ ኢየሱስንና ሌሎችን ለማገልገል አዲስ ሴት ሆና ተለወጠች፡፡ ራሷን ለኢየሱስ የሰጠች ሴት በመሆኗ ኢየሱስ ከሞት ከተነሣ በኋላ ለእርሷ ታየ፡፡ ሌሎች አማኞችም ተቀብለው በሴቶች ቡድን አባል እንድትሆን አደረጓት፡፡ ነፃ መውጣት የሚያስፈልጋችሁ ከምንድነው? እርስበርሳችሁ በመገልገል እግዚአብሔርን እያመሰገናችሁ ናችሁ?